# ጥናት አንድ ሚልኪያስ 1፡1-14 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በእነዚህ አጭር የሆኑ ቁጥሮች ውስጥ የምንመለከተው ነገር፤ እግዚአብሄር አምላክ ለሕዝቡ ያለውን ፍቅር ግልጽ አድርጎ “እኔ ወድጃችኋለሁ” በማለት ሲናገራቸው፤ ሕዝቡ ደግሞ ይህ አባባሉ ግራ እንደገባቸውና ጥያቄ እንደፈጠረባቸው፤ ስለዚህም ደግሞ “እንዴት ወደድከን?” በማለት ስሜታቸውን በመግለጽ ከእርሱ የተለየ አመለካከት እንደነበራቸው እናያለን። እነዚህ ሰዎች ወደዚህ አስተሳሰብ የመጡት፤ ለሰባ ዓመታት በግዞት የኖሩ በመሆናቸው፣ አሁንም ደግሞ ከስደት ከመጡ በኋላ እየኖሩ ያሉት ኑሮ ምናልባትም በአካባቢያቸው ከሚኖሩት ጋራ ሲያወዳድሩት ያነሰ እንጂ የተሻለ ባለመሆኑ፤ እግዚአብሄር ቢወደን ኖሮ የተሻለ እንኖር ነበረ በሚል ሊሆን ይችላል እላለሁ።
2. ቁ4-5ትን በማንበብ ኤዶምያስ ወይም ደግሞ ኤሳው ስለተባለው ሰው ማየት የምችለው መንፈሳዊ ሁኔታ ቢኖር፤ የትዕቢት ነገር፣ እንቢተኛ ልብ እንዳለው፣ እግዚአብሄርን የመዳፈር ነገርና፣ ለእግዚአብሄር ሃሳብና ፈቃድ ያለመገዛት መንፈስ እንደሚነዳው ይታየኛል ነው ለእኔ ግልጽ ሆኖ የሚታየኝ። “እነርሱ ይሰሩ ይሆናል፤ እኔ ግን አፈርስባቸዋለሁ።” በማለት እግዚአብሄር ኤዶምያስን ብቻ ሳይሆን በእርሱ ፈቃድና ሥልጣን ላይ በእንቢተኛነትና በትዕቢት ለሚነሱት ሁሉ ማፍረስ እንደሚችል ነው በዚህ ክፍል የሚናገረው።
3. በዚህ ቁጥር ላይ እግዚአብሄር በራሱ ላይ የደረሰውን በደል ለእስራኤል ሕዝብ ለማስረዳት የተጠቀመባቸውና ማንኛውም ሰው በቀላሉ ሊረዳ በሚችል መንገድ የተጠቀመባቸው ሁለቱ የግንኙነት ዓይነቶች፡ አንደኛው በአባትና በልጅ መሃል ያለው ልጅ አባቱን የማክበር ነገር ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ በባሪያና በጌታ መሃል የነበረው የአክብሮት ሁኔታ ነው። እግዚአብሄር አምላካችን ለዘለዓለም የማይለወጥ አምላክ ስለሆነ፤ ዛሬም የእርሱ ልጅ ነኝ፤ የእርሱ ባሪያም ነኝ የሚሉ ሁሉ ለእስራኤል ልጆች እንደተናገረው ሁሉ እንደ አባትነቱ መከበርን እንደሚጠብቅ፤ እንደ ጌትነቱ ደግሞ መፈራትን እንደሚጠብቅ ልብ ልንል የሚያስፈልግ ሲሆን፤ በጸጋው መዳናችንም ቢሆን ከእነዚህን ነገሮች ነጻ የሚያደርገን እንዳልሆነም መረዳት ጠቃሚ ነው።
4. በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ እግዚአብሄር ከላይ እንደተመለከትነው እርሱ ሆኗል ወይም አድርጋችኋል ለሚላቸው ነገር እነርሱ ሳይታያቸው ሲያስረዳ ይታያል። እዚህ ቦታም ስሜን አቃላችሁታል ሲል ካህናቱ በቤተ መቅደስ መሰዊያ ላይ የተቀደሰ መሥዋዕት ብቻ መቅረብ እንዳለበት እያወቁ የረከሰ ነገር ማቅረባቸው ለስሙ ያላቸውን ንቀት ማሳየታቸው እንደሆነ ነው የሚነግራቸው። ሊቀ ካህናቱ ምናልባት ለሰባ ዓመታት ሁሉ ከቤተ መቅደስ አገልግሎት ሁሉ ስለተለዩ ረስተውት ይሁን አላውቅም ግን በምን እንዳረከሱትም ጥያቄ ሲያቀርቡ፤ እግዚአብሄርም ሳይሰለች ለጥያቄአቸው መልስ በመስጠት በአጭሩ “የእግዚአብሄር ገበታ የተናቀ ነው በማለታችሁ ነው” በማለት ይመልስላቸዋል።
5. “የእግዚአብሄር ገበታ የተናቀ ነው በማለታችሁ ነው።” በማለት እግዚአብሄር ሲናገር፤ ሰዎቹ በአንደበታቸው ሲናገሩ የተሰሙትን ነገር ሳይሆን በተግባር ሲገልጹት የነበረውን ነገር እንደሆነ በቁ8 ላይ አባባሉ ምን ለማለት ፈልጎ እንደሆነ ሲገልጽ፤ የታወረ እንስሳ፣ አንካሳ ወይም በሽተኛ እንስሳን ለመስዋእት ማቅረባቸው በደላቸው እንደሆነ ነው የሚናገራቸው። እንከን ያለበትና የተናቀን ነገር ለሻሾቻቸው ወይም ለአለቆቻቸው ማቅረብ የሚፈሩና የማይገባ ሆኖ ካገኙት፤ እንዲያውማ ለነገሥታት ንጉሥና ለጌቶች ጌታማ ምን ያህል ጥንቃቄ ሊያደርጉ እንደሚገባቸው ለማስተማር ነው።
6. መሥዋዕታቸው በእግዚአብሄር ዘንድ ተቀባይነት እንዳይኖራቸው የሚያደርጉት ተጨማሪ ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡- አቀራረባቸው በንቀት መሆኑ፣ መሥዋእቶቹ ራሳቸው በቅሚያ የመጡ መሆናቸው፣ አንካሶችና የታመሙ እንስሶች መሆናቸው፣ መስዋዕቱን ለእግዚአብሄር ሲያቀርቡም የተቀደሰ በማስመሰል እግዚአብሄርን ለማታለል በመሞከር እንደሆነም ቁ14 ያሳየናል። በቁ14 ላይ ደግሞ ሌላ የምናገኘው ተጨማሪ ሃሳብ፤ እነዚህ ካህናት ሊያቀርቡ የሚችሉት የተሻለ ነገር ስለሌላቸውና አማራጭ ከማጣታቸው የተነሳ እንዳልሆነ ይህ ቁጥር ግልጽ አድርጎ የማታለል ነገር እንደሆነ ይነግረናል።
7. በቁ10 ላይ እንዲያውም ከቁ6 ጀምሮ እግዚአብሄር ከካህናቱ ጋራ በጥያቄና በመልስ ሲያነጋግራቸው እንደተመለከትነው፤ እግዚአብሄር በቤተ መቅደሱ ውስጥ ለማገልገል ካስቀመጣቸው ሰዎች የሚጠብቅባቸው ነገር በመሰዊያው ላይ እሳትን ከማንደድ የዘለቀ መሆን እንደሚኖርበት ሲናገር፤ በተለይም ቁ10ርን ስንመለከት ምን ያህል በሁኔታው እንዳዘነና የመቅደሱን ደጅ የሚዘጋለት አንድ ሰው ቢኖር ደስ እንደሚሰኝ መናገሩ ቅሬታውን ያሳየናል። በዘመናችንም የአገልግሎታችን ተሳትፎ ብቻውን በቂ እንዳልሆነና እግዚአብሄር በሚፈልገው መንገድ ማገልገል እንደሚኖርብን፤ እንዲሁም እግዚአብሄርን ደስ በሚያሰኝ ሕይወት መኖር እንደሚኖርብን ከዚህ መማር እንችላለን።

<u>ጥናት ሁለት ሚልኪያስ 2፡1-17 (ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. የመጀመሪያው እንደሚያደርግባቸው የተናገራቸው ነገር እርግማንን እንደሚልክባቸው ሲሆን፤ በሁለተኛ ደረጃ ሊደርስባቸው ያለው ነገር ደግሞ፤ በኑሯቸው ውስጥ እርግማንን ከመላክም ባሻገር፤ ከከዚህ ቀደም በሕይወታቸው ያዩት የነበረውን በረከት የተባለን ነገር ሁሉ ወደ መርገም እንደሚቀይርባቸውም ተናግሯል። በእነዚህ ሁለት ክፍሎች ውስጥ ስንመለከት፤ በአንደኛው ላይ እግዚአብሄር ደስ የማይሰኝበት ነገር ሲኖር እግዚአብሄር ራሱ በረከት አድርጎ የሰጠንን ነገር እንኳን ወደ መርገም መለወጥ እንደሚችልና፤ በዘዳግሙ ጥቅስ መሰረት ደግሞ እግዚአብሄር ሲፈልግ ለሚወደው ሕዝቡ ጠላት ሊያመጣበት የወሰነውን እርግማን እንኳን ወደ በረከት መለወጥ ስለሚችል የሚያስፈራን ነገር እንደሌለ እረዳለሁ።
2. በቤተ መቅደሱ ውስጥ አገልጋዮቹ ነን የሚሉት ካህናቱ ለእግዚአብሄር እያቀረቡለት ያለውን መስዋእታቸውን በዚህ ቁጥር ላይ "ፋንድያ" በማለት ነው የሚጠራው። እግዚአብሄር በዚህ ክፍል ውስጥ በቤቱ እናገለግላለን እያሉ በራሳቸው መንገድ እየሄዱ ያሉትን ካህናቱን እንዲታረሙና መንገዳቸውን እንዲያስተካክሉ ለማድረግ ማስጠንቀቂያን እንደሰጣቸው ስናይ፤ በሌላ በኩል ግን እግዚአብሄር እያከናወነ ያለው ነገር፤ እየሰጣቸው ያለው ማስጠንቀቂያው ከሌዊ ጋራ አስቀድሞ የገባውን ቃል ኪዳኑን ለመጠበቅና ለማጽናትም ጭምር የሚጠቀምበት መንገድ እንደሆነም ከቁ4 ላይ መረዳት እንችላለን።
3. ይህንን በእግዚአብሄር በራሱና በሌዊ መካከል እንደተገባ አድርጎ በሚልኪያስ በኩል የተናገረውን የቃል ኪዳን ዓይነት እግዚአብሄር አምላክ በቁ5 ውስጥ "የሕይወትና የሰላም ኪዳን" በማለት ይጠራዋል። በቁ4 እና በቁ5 ውስጥ የምንመለከተው በእግዚአብሄርና በሌዊ መካከል እንደተደረገ የተነገረን ቃል ኪዳን በሁለቱም ወገኖች በኩል ከሃላፊነታቸው እንዳላጎደሉ የሚጠቁሙን ሃሳቦች፤ በቁ5-6 ላይ "እነርሱንም ሰጠሁት" በማለት እግዚአብሄር ለሌዊ ህይወትንና ሰላምን እንደሰጠው ሲናገር፤ በሌዊ በኩል ደግሞ "እርሱም አከበረኝ፤ ስሜንም በመፍራት ጸና፣ እውነተኛ ትምህርት በአፉ ነበረ፣ ምንም ዓይነት የሃሰት ነገር በአንደበቱ አልተገኘም፣ ከእኔ ጋራ በሰላምና በቅንነት ተራመደ፣ ብዙዎችንም ከሃጥያት መለሰ" በማለት ሌዊ ደግሞ በበኩሉ ለእግዚአብሄር ማድረግ ያለበትን እንዳደረገ ያሳየናል።
4. በዘመናችን የምናያቸው አንዳንድ አብያተ ክርስትያናት ገንዘብ የሚሰጡትን ሰዎች በተለይም ደግሞ ጠቀም ባለ ሁኔታ ቤተ ክርስትያኒቱን የሚደግፉ ሰዎች ሲኖሩ፤ እነዚያ ሰዎች ምንም ይበሉ፣ ምንም ዓይነት ህይወት ይኑራቸው ወይም ደግሞ ምንም ይድርጉ ስጦታቸውን አያቋርጡ እንጂ ምንም ችግር የለውም፤ በዚህ ክፍል ላይ የምናየው ግን ምንም ዓይነት ቁርባን ወይም ስጦታ ያምጣ፤ እግዚአብሄርን በመታዘዝ የማይሄድ ሰው ከሆነ ከያዕቆብ ድንኳን እንዲወገድ ነው የተነገራቸው። በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የእግዚአብሄርን መሰዊያ በእንባ እየሞሉ እንዳሉ የሚነገርላቸው ሚስቶቻቸው እንደሆኑ ቁ14 በግልጽ ይነግረናል።
5. እግዚአብሄር እንባቸው መሰዊያዬን አጥለቅልቋል እያለ የሚናገራቸውን ሰዎች የጠራባቸው የተለያዩ ስሞች የሚከተሉት ናቸው፡- የትዳር ጓደኛ፣ አጋር፣ የቃል ኪዳን ሚስት፣ የወጣትነት ሚስት የሚሉት ናቸው። ቁ15 የባልና የሚስት አንድነት ከሥጋ አልፎ ልንረዳ በማንችለው መንገድ በመንፈስም አንድነት እንዳላቸው አድርጎ የሚናገር ሲሆን፤ የዚህንም የአንድነታቸውን ምክንያትም ሲናገር፤ ፈሪሃ እግዚአብሄር ያለው ልጅ በእነርሱ በኩል መገኘት እንዲችል እንደሆነ ያሳስባል።
6. እግዚአብሄር የትዳር ጓደኞችን አስመልክቶ በተናገረው ሃሳብ ላይ እንደ ሃሳቡ መጠቅለያ አድርጎ ተጠቅሞበታል ብዬ የማምነውና በቁ13-16 ውስጥ ሁለት ጊዜያት ሰፍሮ የማየው ሃሳብ በቁ15 መጨረሻ ላይና እንዲሁም በቁ16 መጨረሻ ላይ የተናገረው "ስለዚህ በመንፈሳችሁ ራሳችሁን ጠብቁ፤ ታማኝነታችሁም አይጓደል።" የሚለው ሃሳብ ነው። የእግዚአብሄር ሕዝቦች አምላካቸውን በድርጊታቸው ብቻ ያሳዘኑት ሳይሆን ሌላ ያዘነው በአነጋገራቸው ማለትም "በቃላችሁ አታክታችሁኛል" በማለት በእግዚአብሄር ባህርይ ላይ በመናገር የፍትሕ አምላክ መሆኑን እንኳን የመጠራጠር ንግግርን ያሰሙ መሆናቸውን በመጥቀስ ይነግራቸዋል።
7. ካህናቱ የእግዚአብሄር መልዕክተኞች እንደመሆናቸው መጠን የእግዚአብሄርን ምሪት የሚፈልጉ ሰዎች ወደ እነርሱ ስለሚመጡ በምክራቸው ሊያሰናክሉም ሆነ ወደ ቀና መንገድ ለመምራት ስለሚችሉ ነው። እኛም በአዲስ ኪዳን የንጉስ ካህናት ሆነን የተሾምን ስለሆንና የእርሱ አምባሳደሮች መሆናችንም ስለሚታወቅ፤ ሰዎች እግዚአብሄርን ለመፈለግም ሆነ ኢየሱስን ለማየት ከሕይወታችን፣ ከምንናገራቸው ቃላትና ከአኗኗራችንን ሁሉ ወደ እርሱ የሚጠቁማቸው ሳይሆን ማሰናከያና እንቅፋት እንዳንሆንባቸው በጥንቃቄ መመላለስ እንደሚኖርብን ከብሉይ ኪዳን ካህናት መማር እንችላለን።

# <u>ጥናት ሶስት ሚልኪያስ 3፡1-4፡6 (ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. በሚል 3፡1-4 ውስጥ የምንመለከታቸው ሁለቱ መልዕክተኛ በመባል የተጠሩት በተለይም በአንደኛው ቁጥር ላይ ስናይ፤ በመጀመሪያ “መልዕክተኛዬን እልካለሁ” ተብሎ የተነገረለት መጥምቁ ዮሐንስ ሲሆን፤ በዚያው ቁጥር ውስጥ በመቀጠል “መልዕክተኛ ይመጣል” የተባለለት ደግሞ የእግዚአብሄር መልዕክተኛ የሆነውን ኢየሱስን ነው። በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የምናያቸው የኢየሱስን ማንነት እንደሚያንጸባርቁ አድርጎ ነብዩ የጠቀሳቸው ሁለቱ ነገሮች፡ የእርሱን እንደ አንጥረኛ እሳት መሆንና፤ እንደ ልብስ አጣቢ ሳሙና መሆኑን ነው። ሁለቱም ነገሮች ቆሻሻን የማንጻትና ጉድፍን የማስወገድ ባህርይ ሲኖራቸው፤ የካህናቱ ህይወት መጽዳት የሚያስፈልገው ስለሆነ ያንን ሥራ የመስራት ችሎታ አለው ማለት ነው።
2. የህዝቡ እግዚአብሄርን መስረቅ በህይወታቸው ላይ ያስከተለባቸውን ነገር በአንድ ቃል ብቻ አጠቃልዬ ሳስቀምጠው “እርግማን” ማለት እችላለሁ። በእኔ አመለካከት ያዕቆብ እዚሁ ምዕራፍ ውስጥ እንኳን ከቁ7 ላይ ስንመለከት የእግዚአብሄርን ትዕዛዝና ህግ እንደማይጠብቅ ሁልጊዜም ከመንገዱ ፈቀቅ እንደሚል፤ ከዚህም በተጨማሪ አንዴ ሲታዘዝ ሌላ ጊዜ ደግሞ ሲያምጽ እናገኘዋለን፤ ይህ ሁሉ ሲሆን ግን እግዚአብሄር የቃል ኪዳን አምላክ ስለሆነና ስለማይለወጥ ብቻ ያዕቆብ እስከዛሬ በህይወት መኖር ችሏል፤ ለዚህም ነው የእግዚአብሄር አለመለወጥ ወሳኝ ነገር የሚሆነው እላለሁ።
3. ሕዝቡ የእግዚአብሄርን ትዕዛዛት ከተከተሉና የተባሉትን ካደረጉ የሚደረግላቸው የመጀመሪያ ነገር፡ በረከት ይለቀቅላቸዋል ማለትም የሰማይ መስኮቶች ይከፈቱላቸዋል፣ የተትረፈረፈ በረከትም ይፈስላቸዋል። ሁለተኛው ነገር ደግሞ፡ እርግማኑ ይወገድላቸዋል፤ ይህም በቁ11 ላይ የሰፈሩት ሃሳቦች ተባዩን በመገሰጽ አዝመራቸውን እንዳይበላ ያደርጋል፣ የወይን ተክላቸው ፍሬ አልባ እንዳይሆን ያደርጋል፣
4. እነዚህ የእግዚአብሄር ካህናት ከንቱ እንደሆኑና የጊዜ ማባከንም ነገር እንደሆነ አድርገው የሚናገሯቸው ሁለት አይነት ነገሮች፤ አንደኛው እግዚአብሄርን እናገለግላለን ማለት ከንቱ ነገር እንደሆነ፤ ሌላው ደግሞ እግዚአብሄር የሚፈልገውን ማለትም ሕጉን እየጠበቁ መኖርም ምንም ዓይነት ፋይዳ እንደሌለው ይናገራሉ፤ ይህም ማለት አገልግሎት ማገልገልም ሆነ የጽድቅ ሕይወትን መኖር ምንም ጥቅም እንደሌለው ነው የሚናገሩት። ከዚህ ሁሉ ይልቅ እነዚህ ካህናት ያጓጓቸው የሕይወት ዓይነት በቁ15 ላይ የሚናገሩት፤ ብሩካንስ ትዕቢተኞች እንደሆኑ፣ ክፉ አድራጊዎችና እግዚአብሄርን የሚፈታተኑት ምንም ስለማይደርስባቸው የእነርሱን ህይወት እንደ ተመኙ ነው የማየው።
5. እነዚህ ሰዎች በበሚል 3፡14-15 ውስጥ ይናገሩ የነበሯቸው ነገሮች በሁለት የተከፈሉ ሲሆን፤ አንደኛው እግዚአብሄርን ማገልገል ከንቱ እንደሆነና፤ ሌላው ደግሞ እግዚአብሄር የሚፈልገውን ማድረግ ማለትም ሕጉን መጠበቅም ምንም ጥቅም እንደሌለው ሲሆን፤ በቁ18 ላይ እግዚአብሄር ለሁለቱም የተሳሳቱ አመለካከቶች መልስ ሲሰጥ፤ በመጀመሪያ ደረጃ በጻድቁና በሐጥያተኛው መሃል እንደሚለይ በመንገር አንዱን ጥያቄ ይመልሳል፣ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ እርሱን በሚያገለግለውና በማያገለግለውም መሃል ያለውን ልዩነት ምንም እንኳን ዛሬ ማየት ባይችሉ “በዚያን እለት” በግልጽ እንደሚያዩ በመናገር ይመልስላቸዋል።
6. እነዚህ የእግዚአብሄር ካህናትና አገልጋዮቹ በአካባቢያቸው በሚመለከቷቸው ትዕቢተኞችና ክፋትን በሚያደርጉ ሰዎች ሕይወት ምን ያህል እንደሚቀኑባቸው የተናገሩ ሲሆን፤ እግዚአብሄር ግን ሊያሳያቸው እየሞከረ ያለው ነገር ቢኖር፤ ቀን እንደሚመጣ፤ በዚያን ጊዜም እነዚህ ዓይነት ሰዎች የጥፋት ጊዜ እንደሚሆን፤ ከዚያም አልፎ ከእነርሱ እግር በታችም እንደሚወድቁ ይነግራቸዋል። በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ስለ ትዕቢተኞችና ክፉዎች ሲነገር የምናነበው ጉዳይ መዝሙረኛው ዳዊትም ልክ ይህንኑ የመሰለ እግዚአብሄር አምላክ ከሚናገረው ነገር ጋራ የሚስማማ ሃሳብ ሲናገር ነው የምናየው። ዳዊት እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች ለጊዜው የለመለሙ መስለው ይታዩ እንጂ ድርቀታቸውና ከቦታው መጥፋታቸውም አይቀሬ ነገር እንደሆነ ያረጋግጥልናል።
7. እነዚህ ሁለት ቁጥሮች ማለትም ቁ5 እና ቁ6 ያነጣጠሩበትና የሚናገሩት ብዬ የማምነው ሰው መጥምቁ ዮሐንስ እንደሆነ አምናለሁ፤ ይህንንም ማለት የቻልኩበት ምክንያት በማቴ 11፡14 ላይ እንደምንመለከተው የማቴዎስ ወንጌል ጸሐፊ “…ይመጣል የተባለው ኤልያስ እርሱ ነው።” በማለት ግልጽ በሆነ መንገድ አስቀምጦልናል። ለአራት መቶ ዓመታት ሰፍኖ የነበረው የእግዚአብሄር ለሕዝቡ ያለመናገሩ ዝምታም ለመጀመሪያ ጊዜ ተሰብሮ የምንመለከተው በዚሁ ሰው ማለትም በመጥምቁ ዮሐንስ ነው።
8. በዚህ ቁጥር ማለትም በሚል 3፡16 ላይ ስለ እግዚአብሄር እየተነጋገሩ ያሉትን ሰዎች ጸሐፊው “እግዚአብሄርን የሚፈሩ ሰዎች” በማለት ነው ሲጠራቸው የምንመለከተው። ከዚሁ ቁጥር ከፍ ብሎ በሚል 3፡14-15 ላይ በጊዜው የእግዚአብሄር አገልጋዮች የነበሩት የእግዚአብሄር ካህናት ይናገሩ ከነበሩት የስንፍና አነጋገር የተለየ ነገር ያደረጉትና “እግዚአብሄርን የሚፈሩሰዎች” በሚል የምናውቃቸው ሰዎች ንግግራቸው ያስገኘው ውጤት፡ በመጀመሪያ ደረጃ ንግግራቸው በእግዚአብሄር ዘንድ እንደተሰማ ስናነብ፤ ሌላኛው ደግሞ እግዚአብሄርን ለሚፈሩና ስሙን ለሚያከብሩት በእርሱ ፊት የመታሰቢያ መጽሐፍ እንደተጻፈላቸው እንመለከታለን።